## እኛ ማን ነን?

- እኛ ካካባቢው የተሳሰርን ሰዎች፡ ስለ ጊዝያዊ እስረኛች የምናስብ ቡድን ነን።
- እኛ ደሞዝ የማይከፈላቸው፡ በጋትዊክ ጊዝያዊ እስር ቤት ለሚገኙትን እስረኞች ሁሉ፡ ህይወት የተሻለ እንድትሆንላቸው ሙከራ ለማድረግ ጊዜአችንን የሰጠን ውለንተኞች ነን።
- እኛ ከጊዝያዊው እስር ቤት ይሁን ከኢሚግረሽን ጋር ምንም ግንኙነት የሌለን ነጻ ሰዎች ነን።
- ግማሾቻችን የሃይማኖት ሰዎች፡ ግማሾቻችን ደግሞ ምእመናን አይደለንም።

## ማንን እንረዳለን?

- እኛ ከማንኛውም ጎሳ፣ ቢሄርና ሃይማኖት፡ በጋትዊክ ጊዝያዊ እስር ቤት ለሚገኝና እርዳታ ለጠየቀን ማንንም ሰው እርዳታችንን እናቀርባለን።

## የምናቀርበው እርዳታ ምንድነው?

- እስረኛችን የመጠየቅ እቅድ አቁመናል፤ ማለት አንድ ጠያቂ አባላችንን ከአንድ ግዝያዊ እስረኛ ጋር እንዲተሳሰር እናደርጋለን።
- ጠያቂዎቹ፡ እስረኞችን ለመጠየቅ በሄዱበትን ቁጥር፡ ወዳጅነት፣ አሳቢነት፣ መከባከብና ድጋፍ ያበረክታሉ። ጠያቂዎቻችሁን የፈለጋችሁትን ነገር፡ በተለይ ስለ ችግሮቻችሁን ማነጋገር ትችላላችሁ። ያዳምጥዋችሁዋል፤ እንዲሁም በማንኛውም ረገድ እናንተን ለመርዳት የተቻላቸውን ያህል ይሞክራሉ።
- ከቦታው የማይሰጡዋችሁ ነገሮች፡ ግን የሚያስፈልጉዋችሁ፡ ትናንሽ ድጋፎች፡ እንደ መተጣጠብያ እንዲሁም አሮጌ ልብስ ልናገኝላችሁ እንችላለን። ከጠቀስናቸውን ነገሮች የሚያስፈልጉዋችሁ ከሆን፡ ሊጠይቃችሁ ለሚመጣውን አባላችን ንገሩት፤ ጠያቂ በመጠበቅ ላይ ካላችሁ ደግሞ ወደ ጽሕፈት ቤት ስልክ ደውሉ።

ከጠበቃችሁ ጋር እንድትነጋገሩም ልንረዳችሁ እንችላለን። የሚደናገራችሁ ነገር ካለ ደግሞ ሊጠይቃችሁ ለሚመጣውን ሰው፡ በናንተ ስም ጠበቃችሁን በስልክ እንዲያነጋግር ልትጠይቁት ትችላላችሁ። አስፈላጊ ሆኖ ከተሰማችሁም ጠበቃ እንድትቀይሩ ወይም አቤቱታ እንድታቀርቡ ልንረዳችሁ እንችላለን። ብዙ የስራ ልምምድ ያላቸው፡ ልታነጋግሩዋቸው የምትችሉ የኢሚግረሽን ጠበቃዎችም እናውቃለን። እንዲሁም፡ ሊረዱዋችሁ የሚችሉ የሌላ ድርጅቶችን መረጃ ልንሰጣችሁ እንችላለን።

## ልንረዳችሁ የማንችለውን

- ከጊዝያዊ እስር ቤቱ ልናስለቅቃችሁ ወይም እንዳይመልስዋችሁ ልንከላከልላችሁ አንችልም።
- ጠበቃዎችም አይደለንም፤ ስለዚህ ስለ ጉዳያችሁ ሕጋዊ ምክር ለመስጠት አንችልም። ሊጠይቅዋችሁ የሚመጡ አባሎቻችንም እንድትለቀቁ ዋስትና ሊያረጋግጡሏችሁ አይችሉም። በዋስትና እንድትለቀቁ የማመልከቻ ፎርም መሙላት ከፈለጋችሁ ግን BID የሚባል ሌላ ድርጅት ሊተባበራችሁ ይችላል። ከሰኞ - ሐሙስ፡ 10 ከጥዋቱ - 12 እኩለ ቀን ይሰራሉ። ስልክ ቁጥራቸው፡ 0207 247 3590 ነው፤ የፋክስ ቁጥራቸውም፡ 0207 247 3550 ነው።
- እኛ ባጀታችን የተወሰነና ያልተደራጀ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነን። ጠያቂ አባሎቻችን ውድ ነገሮች ሊያረጉላችሁ አይችሉም።

## አሰራራችን እንዴት ነው?

- ጠያቂ እንዲመጣላችሁ ከጽሕፈት ቤታችን ጋር በስልክ ከተነጋገራችሁ ወዲህ ስማችሁ በጠያቂ ጠባቂዎችን ስም ዝርዝር ላይ ይመዘገባል።
- ስማችሁ በዝርዝሩ መጀመሪያ ላይ ሲደርስ፡ ጠያቂ ይመጣላችሁዋል፤ አብዛኛውን ባጭር ጊዜ ውስጥ።
- ከእናንተ ጋር አብሮው ልጆች ካሉዋችሁ ወይም ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች ከሆን፡ ወይም የሕክምና ችግሮች ካሉባችሁ ወይም ደግሞ ሁኔታውን መቋቋም በጣም ከከበዳችሁ፡ በስልክ ላነጋገራችሁትን አባላችን ልትነግሩት ይገባችሁዋል። እና ባስቸኳይ ጠያቂ እንዲመጣላችሁ የሚቻል ይሆናል።

## ከጠያቂዎቻችሁ ልትጠብቁዋቸው የምትችሉትን ነገሮች

- አንዴ ጠያቂ ከተላከላችሁ እና በጋትዊክ እስር ቤት እስካላችሁ ድረስ፡ አብዛኛውን ጊዜ፡ በየሳምንቱ እየመጡ ይጠይቁዋችሁዋል።
- ሊጠይቁዋችሁ የማያስችላቸውን ሳምንት ሲኖር፡ አስቀድመው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ለብዙ ሳምንት ሊጠይቁዋችሁ የማይችሉ ከሆን ግን፡ እየመጣ የሚጠይቃችሁ ሌላ ሰው ማዘጋጀት ይችላሉ። ማንኛውም ችግር ቢያጋጥማችሁና ከሚጠይቃችሁ ሰው ጋር ለመገናኘት ካልቻላችሁ ደግሞ ወደ ጽ/ቤት ስልክ መደወል ይኖርባችሁዋል።

## አስተርጓሚዎች

- ጠያቂ አባሎቻችን ሁሉንም ቋንቋዎች ተናጋሪ ባይሆኑም፡ ብዙ ቋንቋዎች ይናገራሉ። ጠያቂ ካስፈለጋችሁና እንግሊዝኛ የማትናገሩ ከሆን፡ ቋንቋችሁ የሚናገር ጠያቂ እንዲገኝላችሁ እንሞክራለን። እንድናገኝላችሁ የማንችል ከሆን ግን፡ ልንጠይቃችሁ እዚያው በምንመጣበት ሳዓት፡ አንዱ ከወዳኞቻችሁ ሊያስተረጉምልን ይችል ይሆናል።

## እሙንነት

- ግላዊነታችሁ በጥንቃቀ የምንይዘው ጉዳይ ነው። እናንተ ፈቃድ ካልሰጣችሁት በስተቀር፡ ጠያቂያችሁ ከቡድናችን ውጭ ስለናንተ ከማንም ሰው ጋር አይነጋገርም።

## አቤቱታና ችግሮች

- በምንሰጣችሁ አገልግሎት ማንኛውም አስተያየት ወይም አቤቱታ ካልዋችሁ፡ እባካችሁ የጽ/ቤቱን ሰራተኞች አነጋግሩ። ችግሩን ያጠኑታል፤ የአቤቱታ መምሪያችንን በመከተልም፡ ስለሚያሳስባችሁን ነገር መልስ ለማግኘት ይሞክራሉ።

## ሕጋዊ ችግሮችና ምክር

- ከታሰራችሁ፡ ነጻ ሕጋዊ ምክርና ውክልና የማግኘትን መብት አላችሁ። ሁሉም ጠበቆች እውነተኞች

አይደሉም። አንዳንዶቹም ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁዋችሁ ሊሆኑ ይችላሉ። በጠበቃዎቻችሁ ላይ ጥርጣሬ ካሳደራችሁ፡ ጠያቂውን ወይም ጥሩ ስም ያተረፉትን ሕጋዊ የምክር ድርጅቶችን አነጋግሩ። በዋናው ላይብረሪ የብቁ ጠበቆችን ስም ዝርዝር አለ።

▪ ከጠበቃችሁ ጋር ማንኛውም ችግር ካጋጠማችሁ ወይም ጠበቃ ከሌላችሁ፡ ወደ ቦታችሁ የሚመጡትን የሕግ አማካሪዎችን እንድታነጋግሩ እናሳስባችሁዋለን። በነጻ ብቁ ሕጋዊ ምክር ይሰጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ እዚያው እቦታችሁ በሳምንት 2 ጊዜ ይመጣሉ። ምክር እንዲሁም የሕግ ውክልና ሊሰጥዋችሁ ይችላሉ። በዚሁ ጉዳይ በበለጠ ኢንፎርመሽን ካስፈለጋችሁ እዚያው በቦታው ለሚገኙትን ሰራተኞች መጠየቅ ትችላላችሁ።

**አስቸኳይ ሁኔታ፡** (ለምሳሌ፡ ሊያባርሩዋችሁ ዝግጅት ካደረጉ) ወደ RLC ስልክ መደወል ትችላላችሁ፤ ማታም ቅዳሜና እሁድም፡ ስልክ ቁጥር - 07831 598 057።

## የሕክምና ችግሮች

▪ ማንኛውም የሕክምና ችግሮች ካላችሁ፡ ሕክምና ክፍል ሄዳችሁ ዶክቶርን አነጋግሩ። ጤናችሁን በሚመለከት ማንኛውም ስጋት ሲያድርባችሁ ደግሞ፡ ዶክቶር በሚመጣበት ጊዜ የመታከምን መብት አላችሁ።

▪ በሚደረግላችሁ ሕክምና እርካታ ካላገኛችሁ ወይም ሕክምናው ካልረዳችሁ ግን ዶክቶሩ ጋር ተመለሱና ንገሩት።

▪ በተደረገላችሁ ሕክምና አሁንም ገና ካልተደሰታችሁ ደግሞ፡ ጠበቃችሁን ማነጋገር ትችላላችሁ። እንዲሁም ለጠያቂው ንገሩት። እንዲሁም በይፋ አቤቱታ ማቅረብ ትችላላችሁ (የሚቀጥለውን ተመልከቱ)።

## በጊዝያዊ እስር ቤት፡ መብቶቻችሁ

በጊዝያዊ እስር ቤት እስካላችሁ ድረስ፡ በጊዝያዊ እስር ቤት ሕግ መሰረት፡ መብትና ልዩ መብት አላችሁ። በቦታው ላይ ከሁለት ቀኖች በላይ ከሰነበታችሁ፡ ይህ ድሮ የተነገራችሁ ሊሆን ይችላል። ቢሆም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፥

**የአብየቱታዎችን ደንብ፡**

የአቤቱታ አቀራረብን ደንብ በሚመለከት ኢንፎርመሽን ማግኘት ይገባችሁዋል። አቤቱታችሁ (ስታቀርቡ) ይጠናል፤ ሆኖም በጊዝያዊው እስር ቤት በምትቆዩበትን ጊዜ ሕጋዊ ይሁን የሕክምና መብታችሁን አይነካም።

**የገላ መተጣጠብያ፡** የጥርስ መፋቅያና የጥርስ ሳሙና፣ የገላ ሳሙና፣ ሻምፖ፣ የጢም ቅባት፣ የገላ ፎጣዎችና ሌሎች ተፈላጊዎችን በነጻ ማግኘት ይገባችሁዋል።

**ገንዘብ፡** በየዕለቱ ትንሽ የኪስ ገንዘብ አበል እንዲሰጣችሁ መብት አላችሁ። ገንዘቡን እንዴት እንደምትወስዱ፡ የማእከሉ ሰራተኞች ማሳወቅ ይገባቸዋል።

**የኢሚግረሽን ራፖር፡** ከታሰራችሁ ወዲህ፡ ከኢሚግረሽን፡ ለምን አሁንም ገና መታሰራችሁን የሚገልጽ የእርምጃ ራፖር በየወሩ ማግኘት ይገባችሁዋል። ይህ ካልተሰጣችሁ፡ በቦታው ካሉትን ኢሚግረሽን፡ ራፖርን ለማግኘት እንዲተባበሩዋችሁ፡ ቀጠሮ እንዲደረግላችሁ ጥያቄ አቅርቡ።

## ወደ ሌላ ጊዝያዊው እስር ቤት ከቀየሩዋችሁ

▪ ወደ ሌላ ጊዝያዊ እስር ቤት ወይም እስር ቤት ከቀየሩዋችሁ፡ ጠያቂ አባሎቻችን ሊጠይቁዋችሁ አይችሉም። ይሁን እንጂ እርዳታ ሊሰጡዋችሁ የሚችሉ ሌሎች ጠያቂ ቡድኖች ይኖራሉ። ለምሳሌ፥

▪ **Harmondsworth and Colnbrook** – London Detainee Support Group, Tel. 020 7226 3114 / 0800 587 2096

▪ **Dover** – Dover Visitors Group, Tel. 01304 242755

▪ **Haslar Holding Centre** – Haslar Visitors group, Tel. 023 9283 9222

▪ **Yarls Wood Detention Centre** – Yarls Wood Visiting Group, Tel. 01234 708710

ወደ ሌላ ቦታ ከቀየሩዋችሁ፡ እና ጠያቂ እንዲመጣላችሁ ከፈለጋችሁ፡ እባካችሁ ስልክ ደውሉልንና ልንረዳችሁ እንሞክራላን።

## ከተለቀቃችሁ ደግሞ

▪ ከተለቀቃችሁ፡ ግን የምትሄዱበትን ቦታ ከሌላችሁ ወይም ድጋፍና ምክር ካስፈለጋችሁ፡ ከዚህ በታች የሚጠቀሰው ድርጅትን አነጋግሩ።

**Refugee Council's One Stop Service:**
240-250 Ferndale Road, Brixton, London SW9 8BB, Tel. 0207 346 6700


GDWG OFFICE:
225 Three Bridges Road,
Crawley, West Sussex, RH10 1LG
**ስልክ**: (01293) 434350. **ፋክስ**: (01293) 434351

ነጻ ስልክ – 0800 389 4367


ጽ/ቤታችን ከሰኞ– ዓርብ፡ ከ9፡30 ከጥዋቱ – 5፡30 ከሰዓት ክፍት ነው፤ እንዲሁም ምንጊዜም ቢሆን መልእክት መተው ትችላላችሁ። እኛም ባስቻለን መጠን ወዲያው እንደውልላችሁዋለን። እባካችሁ የስማችሁን ፊደል በዝርዝር (በእንግሊዝኛ) ተናገሩ፤ የክፍላችሁ ቁጥርም ተው።


የስራ አስተባባሪ፡ ኒክ ኤይዲ

ረዳት ሰራተኛ፡ ኣና ፒንካስ
ረዳት ሰራተኛ፡ ሉዊስ ፐይም


# ጋትዊክ ጊዝያዊ እስረኞች በጎ አድራጎት ቡድን


የችሮታ መመዝገቢያ ቊ. 1124328
የተወሰነ ኩባንያ በዋስትና ቊ. 4911257


# መረጃ ለጊዝያዊ እስረኞች

Amharic